PANORAMA # XIV

# የትዝብት አድማስ

ጥር 14 2000 ዓም

## በጠላቶቹ የተከበበ ሠራዊት

በአራቱም ማዕዘናት በጠላቶቹ የተከበበና ጠንከራ እምነትና አንድነት የሌለው ሠራዊት ከሌላው ሠራዊት በተለየና በከፋ መልኩ ከሥነአዕምሮ ጭንቀት ላይ ይወድቃል፡፡ ሰማዩ ይደፋበታል፥ ምድሩ ይከዳዋል፡፡ ሜዳው ገደል፥ቀኑ ጨለማ ፥ዙሪያው ባድማ ይሆናል፡፡ መተማመን ይሰወራል፡፡ ቅጥ-አምባሩ ይጠፋበታል፡፡ ጥላውን ይፈራል፡፡ አዛዦቹ ይጣላሉ፥ ሽማምንቱ እርስ በእርስ ይራኮታሉ፥ ይነታረካሉ፡፡ አዛዥና ታዛዥ የሚባል አይኖርም፥ ወታደሮቹ ያምፃሉ፥ይከዳሉ፡፡ የአለቆቻቸውን ትዕዛዝ አያከብሩም፡፡ ወታደራዊ ሥነስርዓት ይጠፋል፡፡ መተባበርና መረዳዳት ያከትማል፡፡ የዕዝ ሰንሰለት ይበጣጠሳል፡፡ እርስ በእርስ መጠባበቅና መጠራጠር ይሰፍናል፡፡ አንዱ ሌላውን አያምንም፡፡ ከጠቅላይ መምሪያ ጋር ግንኙነቱ ይቋረጣል፡፡ በጣም የሚያስፈልገው የወገን ጦር ርዳታና ድጋፍ ሁሉ ሊያገኝ ከማይችልበት ደረጃ ይደርሳል፡፡ የውጊያ መንፈስ ይጠፋል፡፡ በዚህ ዓይነት ቀውጢ ሁኔታ ውስጥ የወደቀ ሠራዊት በመጨረሻዋ ሰዓት ሊኖረው የሚችለው ምርጫ ሁለት ብቻ ይሆናል፡፡ አንደኛው ምርጫ ነጭ ጨርቅ እያውለበለቡ፥ ለጠላት ሠራዊት እጅ እየሰጡ መማረክ ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ፥ የተከበበትን ምሽግ ሰባብሮ በመውጣት ከባቢውን ጦር እያርበተበቱ መረፍረፍ፥እያጨዱ መታጨድ፥ እየጣሉ መውደቅ፥ እየተናነቁ መሰዋት፥ እየቆራረጡ ለአሞራ መስጠት፡፡ ወይምየአሞራ ሲሳይ እየሆኑ፥ መቅረት ይሆናል፡፡ በጥንቷ ኢትዮጵያም " እየቆረጠ፥ሰጠው ላሞራ" የተባለውም በዚህ መሬት ቃጤ በሚሆንበት ወቀት ነበር፡፡ አባባሉ ለዋዛ አልነበረም፡፡

ይህ ክስተት በወታደራዊ ሳይንስና የጦርነት ታሪክ ውስጥ የነበረ፥ ያለና ወደፊትም ሊኖር የሚችል መሆኑን ለማስታወስ የሚደረግ ጥረት ነው ለማለት ቢቻልም፥ክስተቱ ግን በወታደራዊ ሕይወት ብቻ ተወስኖ የሚቀር አይሆንም፡፡ ይህ ሀቅ በአምባገነን ሥርዓት ውስጥ ጎልቶ የሚታይ ክስተት ነው፡፡ ለዚህ ክስተት እንደ ጉልህ ማስረጃ የሚጠቀሰው፥ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ለመሆኑ አንድና ሁለት የሚባል አይደለም፡፡ በተለይም ደግሞ፥ ዛሬ፥ በምኒልክ ግቢ የመሸጉት የወያኔ መሪዎች ዙሪያውን በጠላት ጦር እንደተከበበ ሠራዊት ዓይነት ሁኔታ ላይ እንደወደቁ ማንም ሳይነግራቸው እነርሱ እራሳቸው በሚገባ ያውቁታል፡፡ እንደ ቆሰለ አውሬ እየተቆለጨለጩና በአሮጌ ግንብ ውስጥ ብቻዋን እንደምትቅለበለብ ድንቢጥ የጭንቀት ህይወት እንደሚመሩ፥ አይክዱትም፡፡ በመጨረሻዋ ሰዓት የሚወስዱትን እርምጃ ግን ገና አልወሰኑም፡፡

ይህ ማለት ግን፥ ወደፊት ሊወስዱት ላቀዱት ርምጃ የሚያደርጉትን መሰናዶ ከማድረግ ይዘናጋሉ ማለት አይደለም። ለዝግጅታቸው ዋናው ምክንያትም፥ በመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን፥ ነፃ አውጥተንሃል ብለው በስሙ በሚነግዱበት በትግራይ ሕዝብ ጭምር የተጠሉ መሆናቸውን በሚገባ መረዳታቸው ነው። ከዚህም በቀር ለማምለጫቸው የሚሆናቸውን በቂ ተመክሮ ከመንግሥቱ ኃይለማርያም ሽሽትም ያገኙት ስለሆኑ፥ ይህ ተመክሮ በመጨረሻ ለሚወስዱት ርምጃ ሳይጠቅማቸው የሚቀር አይመስልም። መለስና ግብረ አበሮቹ፥ በመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ የተጧሉና የተወገዙ ቢሆኑም ፥ ለሆዱ ያደረውና ለጊዜው " በልቸ ልሙት" ብሎ የወሰነውን ክፍል፥ እርዳታ ተነፍጓቸዋል ማለት አይደለም። ግን ይህ ክፍል ከመጤፍ ሊቆጠር የሚገባው ክፍል ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም፥ይህ ክፍል በቀውጢው ሰዓት እንደ ነጋበት ጅብ እግሬ አውጭኝ ብሎ የሚፈረጥጥ መሆኑ ስለሚታወቅ ነው። አንድ ነገር ግን መረሳት የለበትም። ይኸውም፥ ይህ ክፍል ለአለፉት ሦስት ተፈራራቂ ሥርዓቶች መልኩን እየለዋወጠ እንዳገለገለ ሁሉ፥ወደፊትም ለመጭው አራተኛ መንግሥት ሰብዕናውን እንደ እስስት እየቀያየረ ግልጋሎትን ለመሸጥ የሚዘጋጅ መሆኑን ነው። የነመለስ ዜናዊ ዕድሜ እንዲረዝምላቸው የሚመኝና የሚፀልም ሌላ አቆብቋቢ ክፍል መኖሩንም መዘንጋት አይገባም፡ ይህ ክፍል ደግሞ የራሱ የሆነ የፖለቲካ ሰሎ አለው። የነመለስ ዜናዊን መንግሥት ኢትዮጵያዊ አጀንዳ እንዲኖረው በማድረግ አብሮ መስራት ይቻላል ከሚል የፖለቲካ ሂሳብ በማስላት፥ " ሎሌ በአፍላው የአህያ መዥገር ይከላል" ዓይነት አገልግሎት ለማበርከትና ለሚቀጥለው የወያኔ ምርጫ የዳንኪራ ድመቀት ለመስጠት የተዘጋጀ መሆኑን ነው። በዚህም ተባለ በዚያ፥ ነገሩ "ዝንብ ቢጠራቀም ወስከምቢያ የሚከፍት አይሆንም" ነው። ምርጫምተባለ የጥገና ለውጥ፥የሀገሪቱን መሠረታዊ ችግሮች መፍታት ቀርቶ፥ መቅረፍ አይችልም። የወያኔና የግብረ አበሮቹ መፍጨርጨር እንደዚሁ፥የኢትዮጵያን መሠረታዊ የፖለቲካ ዕውነታ ሊለውጠው አይችልም። የኢትዮጵየን የፖለቲካ ህይወት በመሠረታዊ መልኩ ሊለውጠው የሚችል የመላው ሕዝቧ ትግልና ውሳኔ ብቻ ነው።

ይህ እንደቆሰለ አውሬ የሚቅለበለበው ጠባብ ብሄረተኛ ድርጅት፥ በአሁኑ ወቅት አጥብቆ የሚፈራው የምልዐተ ሕዝቡን ነጎድጓዳዊ ቁጣና ቅጣት ነው። ይህ ሁኔታ ደግሞ ዘግይቶም ይሁን ፈጥኖ እንደሚመጣበት በሚገባ ያውቀዋል። ከዚህ ከማይቀረው የሕዝብ ቁጣ ለመማምለጥ እንዲያስችለው ይጠቅመኝ ይሆናል ብሎ የሚያስበውን ማነኛውንም ዝግጅትና የማምለጫ መንገድ እንደሚያሰናዳ መገመት የሚያስቸግር አይመስልም። " መለበሚያ አትንሳኝ መለበሚያ ግን አታድርገኝ" እንደሚባለው፥ ወያኔ፥ ከደርግ ድንቁርና የሚያስፈልገውን መለበሚያ ስላገኘ የማምለጫውን መንገዶች ሁሉ በቅድመ-ዝግጅት ሂደት ውስጥ እንደሚያስስ ግን የማይጠበቅ አይሆንም። የደርግን ድንቁርና ለማውሳት የተገደድነው፥አንድ ዓቢይ ቁም ነገር ለማስታወስ ብቻ ነው። ይህንንም ስንል በደርግ ሥርዓተ ዘመን የተፈፀመውን ብሔራዊ ወንጀል ሁሉ ለመዘርዘር ፍላጎቱም፥ ጊዜውም ሆነ ተልዕኮ የለንም ለማለት ነው። ብቻ አንድ በታሪክ ግንዛቤ ሁሉም ሊዘክረውና ሊከትበው

የሚገባውን ማስታወሻ ግን አስምረንበት ማለፍ እንሻለን። ደርግ የኢትዮጵያን ዕውነተኛ ልጆቿን ያለመታከት ሲመትር፥ ቀንደኛ ጠላቶቿን ግን በአርምሞ ይመለከታቸው ነበር። ለኢትዮጵያ አንድነት፥ታላቅነት፥ ዕድገትና ብልፅግና፥ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና ለዜጎቿ አንድነት የቆመውን ሁሉ ያለ ሀኬት እያሳደደ ሲጨፈጭፍ፥ የኢትዮጵያ ቀንደኛ ጠላቶች የሆኑትን እነ ወያኔን በጫጉላ ቤት አስገብቶ ያሸሞነሙናቸው ነበር። ያ ሁሉ ወጣት፥ ሽማግሌ፥ ሀገር ወዳድ አዛውንትና ምሁራን፥ የሃይማኖት መሪዎችና፥ እንዲሁም ሀገር ወዳድ ጀኔራል መኮንኖችና የሀገር መከታ የነበረውን የመከላከያ ሠራዊት ሁሉ መትሮ መትሮ ሲጨርስ፥ በሀገር ገንጣዮችና አስገንጣዮች ላይ ግን ለዘብተኛ የሆነ አቋም ይወስድ ነበር። በአጭሩ፥ ደርግ እንደ አገዛዝ፥ የኢትዮጵያን ስትራተጂያዊ ወዳጅና ጠላት የመለየት ዕውቀቱም፥ችሎታውም፥አርቆ አስተዋይነቱም ሆነ ፍላጎቱ ያልነበረው ገልቱ የገልቱ ስብስብ ነበር። ሩሲያ ሰራሽ በሆነው ጦር መሳሪያ ዙሪያ ሆኖ ዳንኪራ መርገጥ ለኢትዮጵያ አለመፈየዱን እንኳ ዛሬም ቢሆን የሚረዱት አይመስልም። እንዲያው ተሳስተው እንኳን ፥ በአንደምታ ሊገነዘበው ይችል ነበር አለማለት ቢቃጣም፥ የሀገሪቱን የወደፊት ዕጣ ፈንታ ምን ሊሆን ይችላል? የሚለውን እንኳ አስተውሎ ለማየት የፈለገ አንድም ባለሥልጣን አልነበረም ማለት ይቻላል። ይህ ሁኔታ ለነወያኔ ሰፊ ጊዜና ዕድል ስጥቷቸው ዓላማቸውን ከግቡ ለማድረስ አስችሏቸዋል። ዛሬ፥ይህን ሁኔታ ወያኔዎቹ በሚገባ ለመረዳት በቅተው፥ ከደርግ ስህተት በመማር እነርሱም ያንን ስህተት በተመሳሳይ መልኩ እንዳይፈጽሙት ይህ ነው የማይባል ጥንቃቄና ሰፊ ውይይትም በማድረግ ላይ እንደሚገኙ የውስጥ አዋቂ ምንጮች ይናገራሉ። ለምሳሌ እኛ በፈፀምነው ስህተት ምክንያት ጦሱ፥ እኛ ከተወገድን በኋላ የቱን ያህል የእኛን ወገኖችና ደጋፊዎች ሊጎዳ ይችላል? ብለው በመጠየቅ አስፈላጊውን መልስ ብቻ ሳይሆን፥ የመከላከያ ዘዴያቸውንም በማድረግ እንደሚፍጨረጨሩ ንቆ መተውመ አይገባም። በኋላ ይህ አመለካከትና ንቀት፥ ናቂ ወዳቂ የሚያሰኝ መተረቻ ሊያሰተርፍ ይችላል። በደርግ አነሳስ ዘመን " ደርግ አንድ ሐሙስ ቀርቶታል" የሚለው ፌዝና፥ ወያኔ የት ትደርሳለች ሲባል የነበረው ፉተታ ምን ሀቅ እንዳስመሰከረ ተቃዋሚ ኃይሎች ሊገነዘቡት ይገባል።

ከሳሃራ በረሀ በታች ካሉት የአፍሪካ ሀገሮች መካከል ተወዳዳሪ ያልነበረውን ያን የመሰለ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት ያን የመሰለ ዕድል የገጠመው፥ ዙሪያውን በውስጥና በውጭ ጠላቶች የተከበበ የነበረ መሆኑን፥ በውጊያው ላይ በአዋጊነት ቦታ የነበሩ በርካታ የጦር መኮንኖች፥ ዛሬ በማስረጃ በተደገፉ መጽሐፍት ለታሪክ ማስታወሻነት እያቀረቡት ይገኛሉ። በአሁኑ ወቅት ወያኔም በበኩሉ፥በጠላት እንደ ተከበበ ሠራዊት በምኒልክ ግቢ ምሽጎ በመቅለብለብ ላይ እንደሚገኝ ምንም ጥርጥር ሊኖር አይችልም። ይህንን ሐቅ ለማስተባበል የፖለቲካ ትንታኔ የሚያሻውም አይደለም። የወያኔ መሪዎችም ይህንን ከበባ ተገንዝበውታል። ከሁለት ምርጫዎች የትኛውን እንደሚወስድ የሚያውቁት እነርሱ ራሳቸው ሊሆኑ ቢችሉም፥ ሀሞቱም፥ ድፍረቱም፥ አቅሙና ብቃቱ ኖሯቸው፥ የማይቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጣና ቅጣት ሲመጣ፥ከምሽጋቸው

*ወጥተው÷የመከላከያ መስመራቸውን ስለው÷ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለመመከት ይችላሉ ተብለው አይጠበቁም። ይህ ድፍረትና ጀግንነት÷ የታደለው÷ ለመቅደላው÷ ለመተማው÷ ለደጎአሌው÷ ለአድዋው÷ ለወልወሉና ሌሎቹ የጦር ሜዳጀግኖች የሚሰጥና በጊዜያችንም በቆራጥ የኢሕአፓ ልጆች የተንፀባረቀ የተለየ ዕድል እንጅ÷ ለነመለስ ስብስብ የሚታደል አይደለም። እነ መለስ ዜናዊ ለኢትዮጵያ ካላቸው ጥላቻ የተነሳ÷ በቀውጢው ሰዓት÷ አጥፍተው መጥፋትን በአማራጭ ሊያዩት ይችላሉ የሚል የጥቂቶች አመለካከት ቢኖርም በመጨረሻዋ ደቂቃ ሊወስዱትየሚችሉት ምርጫ ግን ይህ ሳይሆን÷ በሥልጣን በነበሩበት በርካታ ዓመታት ውስጥ ያሸሹትን ሃብት ለመብላት እንዲችሉ÷ ከእነርሱ በፊት የነበረው መንግሥቱ ኃይለማርያም እንዳደረገው ሁሉ÷ ሸሽቶ ከመሂድ የተሻለ ምርጫ ሊኖራቸው አይችልም። በብዙ የታሪክ አጋጣሚዎች እንደተመዘገበው÷ በጠላቱ የተከበበ ዓላማ ቢስ ሠራዊትም የፈፀመው ይህንኑ ነበር።*

*መለስና ግብረ አበሮቹም÷ ቀውጢ ቀን ሲመጣ ሸሽተው እንዲያመልጡ የሚጋብዟቸው የኢትዮጵያን ብሔራዊ ኃብት ያስቀመጡባቸው በርካታ የወጭ ባንኮች አሏቸው። የደርጉ መሪም ያደረገው ይህንኑ ነበር። መለስም÷ “ ሞኝህን ፈልግ÷ መንግሥቱ ኃይለማርያምስ ምን ደረሰበት? ማንስ ነካው? የሚል ጥያቄ ጠይቆ የሚያገኘው መልስ አሉታዊ ስለሚሆንለት÷ ሀገር ጥሎ ለመሸሻ የታሪክ ማጠየቂያ አለው። ከሀዲና አሳፋሪ ፀረ ህዝብ ከመባል ግን መቸም አያመልጥም። ውሎ አድሮም የትም ሆነ የት የሕዝብን ፍርድ መቀበሉ የሚቀር አይደለም። ከታሪክ ትዝብት አኳያ ሲገመገም ደግሞ÷ በጠላቶቹ የተከበበ ሠራዊት ሁሉ÷ ሊታዘንለትም ሆነ ሊታዘንበትም÷ ሊፈረድለትም ሆነ ሊፈረድበት የሚችልበት ሚዛን ይኖራል።*

----------------- /////////////////-------------------------